ኅብረት ለምርጫ(CECOE)
የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ
Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections

**የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)**

**የመጀመሪያ ደረጃ ትዝብት ሪፖርት**
**ግንቦት 26 ቀን 2018 ዓ.ም**
**<u>አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ</u>**

## መግቢያ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)፣ ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም የተካሄደውን 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ የአገር የዜጎች ምርጫ ትዝብት (Citizen Election Observation) ለማከናወን፤ 2,506 ተቀማጭ (Sitting Observers) እና 867 ተንቀሳቃሽ (Mobile Observers) ታዛቢዎችን፣ በአጠቃላይ 3,373 ታዛቢዎችን ከኅብረቱ ማሰማራቱ ይታወቃል። እነዚህ ታዛቢዎች የተመለመሉት ከኅብረቱ 101 አባል ድርጅቶች ሲሆን የኅብረቱ ታዛቢዎች ስምሪት፤ ከትግራይ ክልል፣ በአማራ ክልል ከሚገኙ ስምንት (8) የምርጫ ክልሎች፣ እንዲሁም አከራካሪ ከሆኑ 5 የምርጫ ክልሎች ውጭ ባሉ የምርጫ ክልሎች የተከናወነ ነው። ይህ የስምሪት ስልት በየክልሎቹ ያለውን የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት መሠረት ባደረገ ተመጣጣኝ (proportional) የትዝብት ዘዴ ላይ የተመሠረተ ነው።

የኅብረቱ ተቀማጭ ታዛቢዎች በተመደቡባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከንጋቱ 11፡30 ሰዓት ጀምሮ የጣቢያዎቹን አደረጃጀትና አከፋፈት፣ የድምፅ

አሰጣጥ፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት፣ የድምጽ ቆጠራ ሂደት፣ እንዲሁም በጣቢያ ደረጃ የተከናወነውን ይፋዊ የውጤት መለጠፍ ሂደት ታዝበዋል። በሌላ በኩል፣ እያንዳንዳቸው ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ቢያንስ ስድስት (6) የተለያዩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በመዘዋወር ታዝበዋል።ኅብረቱ ተንቀሳቃሽ እና ተቀማጭ ታዛቢዎችን በማሰማራት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ካቋቋማቸው በጠቅላላ 51,026 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 7,723 ጣቢያዎችን ወይም 15 በመቶ ለመሸፈን ችሏል።

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት የኅብረቱ ተቀማጭ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ላይ በላኳቸው አምስት (5) የድምጽ መስጫ ቀን ሂደቶች (የጣቢያዎቹን አደረጃጀትና አከፋፈት፣ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት፣ የድምጽ ቆጠራ ሂደት፣ በጣቢያ ደረጃ የተከናወነውን ይፋዊ ውጤት መለጠፍን) ላይ የተመሰረተ ነው።

ሪፖርቱ በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን፤ በውስጡ የተካተቱት ዋና ዋና ግኝቶች የተሰነዱት የኅብረቱ ቋሚ ታዛቢዎች ከተሰማሩባቸው 2,506 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ላይ ተመስርቶ ነው። በሌላ በኩል፣ በሪፖርቱ የተዳሰሱት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች የተሰበሰቡት ኅብረቱ ካሰማራቸው ቋሚና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ከተገኙ ሪፖርቶች ነው።

# ክፍል 1፡ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና አከፋፈት

## 1.1. የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙበት ሥፍራ

በምርጫ ህጉ መሰረት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በወታደራዊ ካምፕ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የጤና ተቋም፣ መጠጥ ቤት ወይም ሆቴል፣

የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም የግለሰብ መኖሪያ ቤት ማቋቋም የተከለከለ ነው።

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ 2,490 (99%) ጣቢያዎች በሕግ በተፈቀዱ ቦታዎች መቋቋማቸውን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 16 (1%) ጣቢያዎች በሕግ በተከለከሉ ቦታዎች መቋቋማቸውን ታዝቧል።

## 1.2. ታዛቢዎች ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ገብተው ለመታዘብ መፈቀድን በተመለከተ

የምርጫ ህጉ ከቦርዱ እውቅና የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች በተመደቡበት የድምፅ መስጫ ጣቢያ ገብተው ሂደቱን በነፃነት መታዘብ እንደሚችሉ ይደነግጋል። ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ 2,503 (100%) ያህሉ ያለምንም ገደብ ወደ ጣቢያዎቹ ገብተው መታዘብ ችለዋል።

በተቃራኒው ግን 3 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እንዳይገቡ መከልከላቸው ታውቋል።

## 1.3. በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መክፈቻ ሰዓት የምርጫ አስፈጻሚዎች ተሟልቶ መገኘት

የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሕግ በተደነገገው የመክፈቻ ሰዓት ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ከመከፈታቸው በፊት የምርጫ አስፈፃሚዎች በቦታው መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ይህ የምርጫ ጣቢያው በወቅቱ እንዲዘጋጅ፣ የምርጫ ቁሳቁሶች እንዲደርሱ እና የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሥርዓት ለመጀመር ቅድመ ሁኔታ ነው።

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 2,428 (97%) ጣቢያዎች፣ የኅብረቱ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያ ሲደርሱ የምርጫ አስፈጻሚዎች በቦታው መገኘታቸውን ታዝበዋል።

በተቃራኒው፣ 55 (2%) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች፣ የኅብረቱ ታዛቢዎች ሲደርሱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ከመክፈቻው ሰዓት (ንጋት 12 ሰዓት) በቦታው እንዳልተገኙ ታዝበዋል። በ23 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ ታዛቢዎች እስከ 11፡30 ድረስ አልደረሱም።

## 1.4. ድምጽ መስጠት በሚጀመርበት ሰዓት በጣቢያዎች የተገኙ የአስፈጻሚዎች ቁጥርን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ በ2,377 (95%) ጣቢያዎች ከሶስት (3) በላይ አስፈጻሚዎች በጣቢያዎች ተገኝተው ሥራ መጀመራቸውን ኅብረቱ ታዝቧል። በአንጻሩ በ102 (4%) ጣቢያዎች ሶስት (3) የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸው ሲረጋገጥ፣ በ27 (1%) ጣቢያዎች ከሶስት (3) በታች የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን መታዘብ ተችሏል።

## 1.5. የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆናቸውን ማረጋገጥን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,499 (100%) ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆኖቸውን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ በ7 (0%) ጣቢያዎች የሚገኙ የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆናቸው በግልፅ እንዳልታዩ መታዘብ ተችሏል። በ2,500 ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ማሽጊያዎች መገኘታቸው የታዘብን ሲሆን በ6 ጣቢያዎች ደግሞ የድምጽ መስጫ ማሸጊያዎች አለመገኘታቸውን ታዝበናል።

## 1.6. ሁሉም የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በ2,505 (100%)፣ የቦርዱ ህጋዊ ማህተም በ2,505 (100%)፣ የማይለቅ

የጣት ቀለም በ2,505 (100%)፣ የመራጮች መዝገብ በ2,504 (100%)፣ የቦርዱ ድምፅ መስጫ ሳጥኖች በ2,505 (100%) ጣቢያዎች መገኘታቸው ታዝቧል። በተቃራኒው፣ የውጤት መግለጫ እና ማመሳከሪያ ፎርም በ3 (0%) ጣቢያዎች ላይ አልተገኘም፤ እንዲሁም የቅሬታ ማቅረቢያ እና ምስክርነት መቀበያ ፎርም በ38 (2%) ጣቢያዎች ላይ አለመገኘታቸውን ታዝበናል።

## 1.7. የምርጫ አስፈፃሚዎች የፆታ እና የአካል ጉዳተኝነት ስብጥር በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል በ1,508 (60%) ጣቢያዎች ከ1 በላይ ሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች ሲገኙ፤ በአንጻሩ 793 (32%) ድምጽ መስጫ ጣቢያ 1 ሴት አስፈጻሚ እንደነበረች ታዝበናል። በተቃራኒው በ205 (8%) ጣቢያዎች ሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች እንዳልተመደቡ ታዝበናል።

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል 88 (4%) በሚሆኑት ከ1 በላይ አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚዎች ተገኝተዋል። በሌላ በኩል 247 (10%) ጣቢያዎች ውስጥ 1 አካል ጉዳተኛ አስፈጻሚ መገኘታቸውን ታዝበናል። በአንጻሩ በ2,171 (87%) ጣቢያዎች ደግሞ አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ እንዳልነበረ መታዘብ ተችሏል።

## 1.8. የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የፆታ እና የአካል ጉዳተኝነት ስብጥር በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ በ655 (26%) ጣቢያዎች ውስጥ የድምጽ መስጫ ጣቢያው ኃላፊ ሴት ነበረች። በተመሳሳይ ሁኔታ በ66 (3%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኛ ሴቶች በጣቢያ ኃላፊነት መስራታቸውን፣ በ76 (3%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ አካል ጉዳተኛ ወንዶች የጣቢያ ኃላፊ ሆነው መስራታቸውን ታዝበናል። በ1,709 (68%) ጣቢያዎች የጣቢያው ኃላፊ ወንድ ነበር።

# ክፍል 2፡ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ

## 2.1. ታዛቢዎች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን እንዲታዘቡ መፈቀድን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,479 (99%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎች በድምፅ አሰጣጥ ወቅት ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ እንዳልተጠየቁ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 27 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የኅብረቱ ታዛቢዎች በድምፅ አሰጣጥ ወቅት ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ መጠየቃቸው መታዘብ ተችሏል።

## 2.2. የድምፅ መስጠት አጀማመር

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ በ1,091 (44%) ጣቢያዎች የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከጥዋቱ 12 ሰዓት በፊት መጀመሩን፣ በ1,370 (55%) ጣቢያዎች ደግሞ ከጥዋቱ 12 እስከ 1 ሰዓት ባለው ጊዜ መጀመሩን ኅብረቱ ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 36 (1%) ጣቢያዎች ከጠዋቱ 1፡01 እስከ 3፡00 ሰዓት፣ 3 ጣቢያዎች ከ3፡01 እስከ 6፡00 ሰዓት መጀመራቸውን፣ እንዲሁም በ6 (0%) ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እስከ 6፡00 ሰዓት ድረስ እንዳልተጀመረ ታዝቧል።

## 2.3. በድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ ወይም በ200 ሜትር ርቀት ውስጥ የቅስቀሳ ምልክቶች እና ቅስቀሳዎች መኖራቸውን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ 2,495 (100%) ጣቢያዎች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ወይም በ200 ሜትር ርቀት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ቅስቀሳ ምልክቶች (ፖስተር) ወይም ቅስቀሳዎች አለመከናወናቸውን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 11 (0%) ጣቢያዎች ውስጥ ወይም በ200 ሜትር ርቀት ክልል

ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ቅስቀሳ ምልክቶች፣ ቁሳቁሶች ወይም የቅስቀሳ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ታዝበናል።

## 2.3. የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት እና አመቺነት በተመለከተ

በምርጫ ህጉ መሰረት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሕግ በተፈቀዱ ቦታዎች መቋቋም፣ ለመራጮች በቀላሉ ተደራሽ መሆን እና መሠረታዊ የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘታቸው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት በሥርዓት እንዲካሄድ አስፈላጊ ነው። በተለይ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ለነፍሰ ጡሮች እና ጨቅላ ሕፃን ለያዙ ወላጆች ተደራሽነት መኖሩ የሁሉንም ዜጎች ተሳትፎ ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙበት ስፍራ ለሴቶች ያላቸውን አመቺነትን በተመለከተ ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ 2,383 (95%) ጣቢያዎች ለሴቶች ምቹ እንደነበሩ ጎብረቱ ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 123 (5%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለሴቶች አመቺ እንዳልነበሩ መታዘብ ተችሏል።

የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ያላቸውን ተደራሽነት በተመለከተ፣ ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,353 (94%) ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች ያለ ረዳት በመግባት ድምፅ ለመስጠት አመቺ እንደነበሩና በተቃራኒው 153 (6%) ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆናቸውን ታዝበናል።

ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች መካከል፣ 2,399 (96%) ጣቢያዎች ለአረጋውያን፣ ለነፍሰ ጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃን ለያዙ ወላጆች እና የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች ምቹ እንደነበሩ ታዝበናል። በተቃራኒው፣ 107 (4%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በዚህ ረገድ ችግር እንደነበረባቸው ታዝበናል።

## 2.4. ቅድሚያ ለሚገባቸው መራጮች የተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,351 (94%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሰልፍ አስከባሪዎች ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰ ጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃናት ለያዙ ወላጆች፣ እንዲሁም መለዮ ለለበሱ የመከላከያና የፖሊስ አባላት ቅድሚያ ሲሰጡ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 155 (6%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በዚህ ረገድ ቅድሚያ ለሚገባቸው መራጮች ተገቢው ቅድሚያ እንዳልተሰጠ መታዘብ ተችሏል።

## 2.5. ከኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ውጭ ሀገር ውስጥ ታዛቢዎች መገኘት

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 1,908 (76%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከኅብረቱ ታዛቢዎች በተጨማሪ ሌሎች የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያ ተገኝተው እንደነበር ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 598 (24%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከኅብረቱ ታዛቢዎች በተጨማሪ ሌሎች የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች እንዳልተገኙ መታዘብ ተችሏል።

## 2.6 በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የተከሰቱ ጥቃቶች፣ ሁከቶች፣ ማስፈራርያ ወይም ትንኮሳ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 ጣቢያዎች ውስጥ በ2,503 (100%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በምርጫ አስፈጻሚዎች፣ በታዛቢዎች ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች ላይ ጥቃት፣ ማስፈራሪያ ወይም ትንኮሳ አለመከሰቱን እና በ26 (1%) ጣቢያዎች ውስጥ ወይም አካባቢ ጥቃት፣ ሁከት፣ ማስፈራሪያ ወይም ትንኮሳ መከሰታቸውን ታዝቧል።

## 2.7 በመራጮች መዝገብ ያልተመዘገቡ ወይም መታወቂያ ያልነበራቸው መራጮች

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,368 (94%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሁሉም መራጮች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ የሰፈረ እና የመራጭነት መታወቂያ የያዙ መሆናቸው ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 130 (5%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 ሰዎች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሳይገኝ እና የመራጭነት ካርድ ሳይዙ እንዲመርጡ መፈቀዱ መታዘብ ተችሏል። በ8 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከ10 በላይ ሰዎች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሳይገኝ እና የመራጭነት ካርድ ሳይዙ እንዲመርጡ መፈቀዱ ታዝቧል።

## 2.8 ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሆኖ ድምፅ ያልሰጡ መራጮች

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,458 (98%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሰፍሮ ድምፅ መስጠት የተከለከለ ሰው እንዳልነበረ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 46 (2%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 ግለሰቦች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሰፍሮ ድምፅ መስጠት መከልከላቸው መታዘብ ተችሏል። በ2 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከ10 በላይ ግለሰቦች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሰፍሮ ድምፅ መስጠት መከልከላቸው ተመልክቷል።

## 2.9 ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች የተደረገ እርዳታ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,277 (91%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች ወይም

ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መራጮች በራሳቸው ምርጫ በረዳት እንዲታገዙ ተፈቅዶላቸዋል።

በተቃራኒው፣ 32 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች በራሳቸው ምርጫ በረዳት እንዲታገዙ እንዳልተፈቀደላቸው ታዝቧል። በ197 (8%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ በሰልፍ ላይ ድጋፍ የሚፈልግ መራጭ እንዳልነበረ ተመልክቷል።

## 2.10 ተደጋጋሚ የመራጮች እርዳታ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,187 (87%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከሰብሳቢው ውጭ አንድ ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ ለተለያዩ መራጮች እርዳታ ሲያደርግ እንዳልተመለከተ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 87 (3%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከሰብሳቢው ውጭ አንድ ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ ለተለያዩ መራጮች እርዳታ ሲያደርግ መታዘብ ተችሏል። በ232 (9%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ ድጋፍ የሚፈልግ መራጭ እንዳልነበረ ተመልክቷል።

## 2.11 በምርጫ አስፈጻሚዎች የተሰጠ የድምፅ አሰጣጥ መመሪያ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,487 (99%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎች ስለድምፅ አሰጣጥ ለመራጮች ሲያስረዱ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምፅ እንዲሰጡ ምክር እንዳልሰጡ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 19 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎች ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምፅ እንዲሰጡ ምክር ሲሰጡ መታዘብ ተችሏል።

## 2.12. የማይለቅ የጣት ቀለምን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,413 (96%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እያንዳንዱ መራጭ የማይለቅ የጣት ቀለም ተቀብቶ ድምፅ መስጠቱን ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 87 (3%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 መራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም ሳይቀቡ ድምፅ እንዲሰጡ መፈቀዱ ተመልክቷል።

በ6 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከ10 በላይ መራጮች የማይለቅ ቀለም ሳይቀቡ ድምፅ እንዲሰጡ መፈቀዱ ታዝቧል።

## 2.13. የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማኅተም ማድረግን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,442 (97%) ጣቢያዎች ሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመሰጠታቸው በፊት ማኅተም ተደርጎባቸው እንደነበር ታዝቧል።

በ59 (2%) ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ማኅተም ሳይደረግባቸው ለመራጮች መሰጠታቸው ኅብረቱ ታዝቧል።

በ5 (0%) ጣቢያዎች ደግሞ ከ10 በላይ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ማኅተም ሳይደረግባቸው ለመራጮች መሰጠታቸውን መታዘብ ተችሏል።

## 2.14. የድምፅ አሰጣጥ ሚስጥራዊነትን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ በ2,337 (93%) ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሚስጥራዊነት እንዳልተጣሰ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 151 (6%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 መራጮች የድምፅ አሰጣጥ ሚስጥራዊነት መጣሱን ተመልክቷል።

በ18 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ ከ10 በላይ መራጮች የድምፅ አሰጣጥ ሚስጥራዊነት መጣሱን ታዝቧል። ይህም መራጮችን ተከትሎ ወደ ምስጢራዊ የድምፅ መስጫ ክፍል መግባት፣ ወይም ምልክት የተደረገበትን ወረቀት ለማየት መጠየቅን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ያካትታል።

## 2.15. የድምፅ መስጫ ሳጥኖች አቀማመጥን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ በ2,502 (100%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሳጥኖች በግልጽ በሚታይ ቦታ ተቀምጠው እንደነበር ታዝቧል። በተቃራኒው፣ በ4 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሳጥኖች በግልጽ በሚታይ ቦታ አለመቀመጣቸውን መታዘብ ተችሏል።

## 2.16. የድምፅ መስጠት ሂደት መቋረጥን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,466 (98%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጠት ሂደት በማንኛውም ሰዓት አለመቋረጡን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ በ40 (2%) ጣቢያዎች የድምፅ መስጠት ሂደት መቋረጡን መታዘብ ተችሏል።

## 2.17. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች መገኘትን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 1,635 (65%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያ ተገኝተው እንደነበር ታዝቧል። በሌላ በኩል፣ 871 (35%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያ እንዳልተገኙ መታዘብ ተችሏል።

## 2.18. ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች የተደረገ እርዳታ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,277 (91%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች ወይም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መራጮች በራሳቸው ምርጫ በረዳት እንዲታገዙ ተፈቅዶላቸዋል።

በተቃራኒው፣ 32 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች በራሳቸው ምርጫ በረዳት እንዲታገዙ እንዳልተፈቀደላቸው ታዝቧል። በ197 (8%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ በሰልፍ ላይ ድጋፍ የሚፈልግ መራጭ እንዳልነበረ ተመልክ ;;;;;p;p;ቷል።

# ክፍል 3፡ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋትን በተመለከተ፣

በህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት መዘጋት አለባቸው። ሆኖም በመዝጊያ ሰዓቱ በሰልፍ ላይ የነበሩ በርካታ መራጮች በመኖራቸው ምክንያት ቦርዱ የመዝጊያ ሰዓቱን እስከእኩለ ሌሊት 6፡00 ሰዓት አራዝሟል።

## 3.1. የድምጽ መስጫ ጣቢያ መዝጊያ ሰዓት

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል 313 (12%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ12፡00 ሰዓት በፊት መዘጋታቸውን ታዝቧል። 1,848 (74%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ12፡00 ሰዓት እስከ 1፡00 ሰዓት፣ 104 (4%) ጣቢያዎች ከ1፡00 ሰዓት እስከ 3፡00 ሰዓት፣ እንዲሁም 241 (10%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከ3፡00 ሰዓት በኋላ መዘጋታቸውን መታዘብ ተችሏል።

### 3.2. በመዝጊያ ሰዓት በሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮች

ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 780 (31%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በመዝጊያው ሰዓት በሰልፍ ላይ ሰው እንዳልነበረ ታዝቧል።

በ1,715 (68%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሰልፍ ላይ የነበሩ ሰዎች ሁሉም ድምፅ መስጠት መቻላቸው ታዝቧል። በ9 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ግን በሰልፍ ላይ ከነበሩ ሰዎች ጥቂቶቹ ድምፅ መስጠት እንዳልተፈቀደላቸው ተመልክቷል። በተጨማሪም፣ 2 (0%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሰልፍ ላይ የነበሩ ሰዎች ሁሉም ድምፅ መስጠት እንዳልተፈቀደላቸው መታዘብ ተችሏል።

## ክፍል 4፡ የድምጽ ቆጠራ ሂደትን በተመለከተ

### 4.1. ታዛቢዎች በድምፅ ቆጠራ ሂደት እንዲታዘቡ መፈቀድን በተመለከተ

ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,490 (99%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የጎብረቱ ታዛቢዎች በድምፅ ቆጠራ ወቅት ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ እንዳልተጠየቁ ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 16 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የጎብረቱ ታዛቢዎች በድምፅ ቆጠራ ወቅት ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ መጠየቃቸው መታዘብ ተችሏል።

### 4.2. የድምጽ ቆጠራው የተከናወነበት ቦታ እና ጊዜ

ከጎብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,447 (98%) ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው በድምፅ መስጫ ቀን በምርጫ ጣቢያው መካሄዱን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 59 (2%) ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው በድምፅ መስጫ ቀን በጣቢያው እንዳልተካሄደ መታዘብ ተችሏል።

በተጨማሪም፣ 59 (2%) ጣቢያዎች ቆጠራው ድምጽ በተሰጠበት ጣቢያ እንዳልተከናወነ ታዝቧል።

### 4.3. የድምፅ ቆጠራ መቋረጥ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,446 (98%) ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው ሳይቋረጥ መካሄዱን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 34 (1%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው ሂደቱ መቋረጡን መታዘብ ተችሏል። በ26 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ ቆጠራው በጣቢያው አልተከናወነም።

### 4.4. በድምጽ ቆጠራ ወቅት ጣልቃገብነት ወይም ማስፈራሪያ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,468 (98%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በድምፅ ቆጠራ ወቅት ጣልቃ ገብነት ወይም ማስፈራሪያ አለመኖሩን ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ በ12 (0%) ጣቢያዎች በድምፅ ቆጠራ ወቅት ጣልቃ ገብነት ወይም ማስፈራሪያ መኖሩን መታዘብ ተችሏል። በ26 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ ድምጽ በተሰጠበት ጣቢያ ቆጠራ አለመከናወኑን ታዝበናል።

### 4.5. በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ የተደረጉ ምልክቶችን ማሳየት

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,415 (96%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ መራጮች ያደረጉትን ምልክት በግልጽ በማሳየት መቆጠሩን ታዝቧል።

በተቃራኒው፣ 65 (3%) ጣቢያዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ መራጮች ያደረጉትን ምልክት በግልጽ ሳያሳይ መቆጠሩን ታዝቧል። በ26 (1%) ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ በጣቢያዎች ውስጥ እንዳልተከናወነ ኅብረቱ ታዝቧል።

## 4.6. ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መለየትን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,462 (98%) ጣቢያዎች የምርጫ አስፈፃሚዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለመለየት ወጥ የሆነ አሰራር መከተላቸውን ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 16 (1%) ጣቢያዎች የምርጫ አስፈፃሚዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመለየት ወጥ የሆነ አሰራር እንዳልተከተሉ መታዘብ ተችሏል። በ28 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ በምርጫ ጣቢያ ቆጠራ እንዳልተከናወነ ታዝቧል።

## 4.7. በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ በምርጫ አስፈጻሚዎች የተደረገ ምልክት

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,407 (96%) ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ምልክት ሲያደርጉ እንዳልተመለከተ ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 77 (3%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ምልክት ሲያደርጉ መታዘብ ተችሏል። በ22 (1%) ጣቢያዎች ደግሞ በምርጫ ጣቢያ ቆጠራ እንዳልተከናወነ ተመልክቷል።

## 4.8. ለድምጽ መስጫ ጣቢያው ኃላፊ የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎችን በተመለከተ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,451 (98%) ጣቢያዎች ምርጫ ጣቢያው ሲከፈት፣ ድምፅ ሲሰጥ፣ ቆጠራ ሲካሄድ እና ውጤት ሲገለፅ ለምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የቀረበ ቅሬታ እንዳልነበረ ታዝቧል። በተቃራኒው፣ 55 (2%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ምርጫ ጣቢያው ሲከፈት፣ ድምፅ ሲሰጥ፣ ቆጠራ ሲካሄድ እና ውጤት ሲገለፅ ለምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ቅሬታ መቅረቡ መታዘብ ተችሏል።

# ክፍል 5፡ በድምጽ መስጫ ጣቢያ ደረጃ የሚከናወነውን ይፋዊ የውጤት መለጠፍን በተመለከተ

## 5.1. የውጤት መግለጫ እና ማመሳከሪያ ቅጽ መለጠፍ

ከኅብረቱ ከታዘባቸው 2,506 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል፣ 2,440 (97%) ጣቢያዎች የውጤት መግለጫ እና ማመሳከሪያ ቅጽ ቅጂ ለሕዝብ እንዲታይ በጣቢያው በር ላይ መለጠፉን ታዝቧል። በሌላ በኩል፣ 40 (2%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የውጤት መግለጫ እና ማመሳከሪያ ቅጽ ቅጂ ለሕዝብ እንዲታይ በምርጫ ጣቢያው በር ላይ አለመለጠፉን ታዝበናል። በ26 (1%) ጣቢያዎች ቆጠራው ድምጽ በተሰጠበት ጣቢያ አለመከናወኑን ኅብረቱ ታዝቧል።

# ክፍል 6፡ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ህብረቱ በድምፅ መስጫ ቀን ያቋቋመው የመረጃ ማዕከል በድምፅ መስጫ ሂደቱ ላይ የተለያዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ባሰማራቸው በአጠቃላይ 3,373 ተቀማጭ እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ከታዘቧቸው 7,723 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እነዚህን ጉዳዮች ህብረቱ ካጣራ እና ካረጋገጠ በኋላ ከዚህ እንደሚከተለው ያቀርባል።

1. **በተከለከሉ ቦታዎች የተቋቋሙ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች**: በአዲስ አበባ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሀረሪና በሲዳማ ክልሎች እንዲሁም በድሬደዋ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በድምሩ በ11 ጣቢያዎች በተከለከሉ ቦታዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸውን ታዝበናል።

2. **በጣቢያዎች ውስጥ ወይም 200 ሜትር ርቀት ላይ ቅስቀሳ ማድረግ**: በአዲስ አበባ ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች

በጠቅላላ በ9 ጣቢያዎች ላይ በህግ ከተፈቀደው ውጭ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እና 200 ሜትር ርቀት የቅስቀሳ ተግባራት ታይተዋል።

3. **ታዛቢዎች ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያ እንዳይገቡ መከልከል ፡** በአዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች በሚገኙ 11 ጣቢያዎች ላይ ታዛቢዎች ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያ እንዳይገቡ ተከልክለዋል።

4. **ከምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ውጪ ተደጋጋሚ እና ያለፈቃድ የተደረገ ድጋፍ፡** በአዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ 22 ጣቢያዎች ከምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ውጪ ተደጋጋሚ እና ያለፈቃድ የተደረገ ድጋፍ ተስተውሏል።

5. **የጸጥታ መደፍረስ ፡** በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በ19 ጣቢያዎች ላይ የጸጥታ መደፍረስ ምክንያት የድምፅ መስጠት ሂደቱ ተቋርጦ የነበረ ሲሆን የድምጽ መስጠት ሂደቱ በድጋሚ ቀጥሏል።

6. **ፈቃድ የሌላቸው ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ፡** አማራ፣ ሲዳማና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባን በአጠቃላይ በ4 ጣቢያዎች ላይ ፈቃድ የሌላቸው ግለሰቦች ተገኝተዋል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ህዝብ 7ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ በተለይም በመራጭነት በመመዝገብ እና ድምፅ በመስጠት ላደረገው ንቁ ተሳትፎ እና በተለይ በድምጽ መስጫ ቀን በትዕግስት ተሰልፎ ለመምረጥ ላሳየው ተሳትፎ እናመሰግናለን።

በመቀጠል የህብረት ለምርጫ አባል ድርጅቶች እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ የተሰማራችሁ የህብረት ለምርጫ ታዛቢዎች፣ የህብረቱ ፅ/ቤት ሰራተኞ እና

የመረጃ መዓከል ባለሞያዎች ለሃገራችን የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ለተጫወታችሁት ገንቢ አስተዋፆ ምስጋና እናቀርባለን።

ይህንን ለሀገራችን ወሳኝ የሆነ የምርጫ ሂደት ያስፈፀመውን ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን፤ የምርጫ ሽፋን የሰጡ የሚዲያ አካላትን፤ በምርጫ ትዝብት፣ በመራጮች ትምህርት እና የፖለቲካ ፓርቶዎች ክርክሮችን በማዘጋጀት ለተሳተፉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፤ ለሂደቱ ሰላማዊነት የበኩላቸውን ድርሻ የተጫወቱ የጸጥታ አካላት ለዚህ የምርጫ ሂደት መከናወን ላደረጋችሁት ጥረት ልናመሰግናችሁ እንወዳለን።

በአጠቃላይ ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ምርጫው ከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎ የታየበት፣ በአብዛኛው ሰላማዊ የነበረ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች በከፍተኛ ትጋት የምርጫውን ሂደት ያስፈጸሙበት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ጋዜጠኞች እና ሚድያ ንቁ ተሳትፎ ያደረጉበት እና የጎላ ጉድለቶች ያልተስተዋሉበት እንደነበር ታዝበናል።

የ7ተኛውን ጠቅላላ ምርጫ መጠናቀቅን ተከትሎ ሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የምርጫውን ውጤት በትዕግስት እንዲጠባበቁ እንዲሁም የምርጫውን ውጤት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሲገለጽ ውጤቱን ተቀብለው ሊኖራቸው የሚችሉ ቅሬታዎች ቢኖሩ ባለው የህግ ማዕቀፍ እንዲያቀርቡ ኅብረቱ ጥሪውን ያቀርባል።

**የዚህን ሪፖርት ሙሉ ዝርዝር ህብረቱ በቅርቡ በሚያወጣው አጠቃላይ የትዝብት ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል።**

**እናመሠግናለን!!**

**ግንቦት 26 ቀን 2018 ዓ.ም**